# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 48

ጥር 7 ቀን 2015ዓም (15-01-2023)

እንዳለፈው የታህሳስ ወር ስርጭታችን የዚህን የጥር ወር ዝግጅታችንን የምንጀምረው በወሩ የስም ትርጓሜ ይሆናል።ያለፈውን የታህሳስን ወር ማሰስ፣መፈለግ፣መመርመር ፣መፈተሽ እንደሆነ መግለጻችን ይታወሳል።በዛም ያሰሳና የፍተሻ ወር ያገራችንን ሁኔታ የፈተሽንበት ነበር።ፈትሸንና መርምረን ያገኘነውም ያገራችን ሁኔታ ከድጡ ወደማጡ እዬገባ መሄዱን በብዙ ማስረጃዎች ለማስረዳት ሞክረናል፤መፍትሔውንም ጠቁመናል።

የዛሬውም የጥር ወር የመጀመሪያ ሳምንት ጥንቅራችን ከዚያ የተለዬ አይሆንም፤ምክንያቱም አገራችን ላይ የሰፈነው አደገኛ የጎሳ ሥርዓት የተለዬ ባለመሆኑ ነው።የጎሰኞቹ የሃይል አሰላለፍ እዬተቀያዬረ መጣ እንጂ የተነሱበት ዓላማና ግብ ያው ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አንድነት ዓላማ ነው።ለሃያ ሰባት ዓመት ተደጋግፈው የቆዩ የአንድ ድርጅት፣የኢሕአዴግ አባላት በጥቅምና በሥልጣን እርስ በርሳቸው ለሁለት ዓመት ሲዋጉና ሲያዋጉ የነበሩት የወያኔና የኦነግ ሃይሎች አሁን ላይ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መልኩ ተጋግዘው የጋራ ጠላታችን ነው በሚሉት ሕዝብና አገር ላይ ተነስተዋል።አገራችንን እንደ ዳቦ ቆራርሰው የዬድርሻቸውን በጭቆ ለመሄድ ተስማምተው የመሬት ቅርምቱን ተያይዘውታል።

ወደ ጥር ወር ስያሜ እንመለስና ቃሉ መንጠር ፣ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመነጨ ሲሆን ትርጉሙ ሲብራራ ነጠረ፣ ጠረረ፣ነጻ፣ብልጭ አለ፣ግልጽ ሆነ ማለት ነው።እውነትም ጥር ማለት ብዥታ ለብሶ የነበረው ነገር ጥርት ብሎ በግልጽ የሚታይበት ወቅት ነው።በመሆኑም ነው አሁን ላይ የሥርዓቱ ምንነት ለብዙሃኑ ፍንትው ብሎ መታዬት የጀመረው። በግልጽ የሚሆነውን ለማዬትና ለመረዳት ያልቻለ ቢኖር ከሰውነት ደረጃ የወረደ ብቻም ሳይሆን ከእንስሳም ያነሰ ፍጡር ነው።ሲያርዱት ሲመጡ በዝምታ ቆሞ የሚጠብቅ ወይም እያጨበጨበ ሞቱን በደስታ የሚቀበል ከዬትኛው ህይወት ካለው ፍጡር ተራ እንደሚመደብ ግራ ያጋባል።የእንስሳቱን አልሞት ባይ ተጋዳይነት ስናይ በሰው ደረጃ የተመደቡትን የነለጥ ይበሉን ዝምታ የምንመዝንበት ሚዛኑ ጠፍቶብናል።የቁም ሙት የሚለው መጠሪያ ተስማሚ ሆኖ አግኝተነዋል። የሚሹትን አግኝተው ፣ኮርተውና ተከብረው ሊኖሩ የሚችሉበት አገር በአደጋ ላይ ወድቆ ሰላም ሲጠፋ ፣ሕዝብ ሲገደልና ሲፈናቀል እያዩ ከወንጀለኞች ጎን ተሰልፈው ለጥቂት ስጦታ፣ለቤትና ቁራሽ መሬት የሚያጎበድዱትን ስናይ ይህ እራስ ወዳድነት ከዬትና ለምን እንደመጣ ስናስበው ግራ ያጋባል።ለሆድ አደሮቹ ያልተገለጸላቸው ቢኖር የሚያገኙት ቤትና ገንዘብ ከራሳቸው ወገን ፣ከህብረተሰቡ በውድም ሆነ በግድ የተሰበሰበ ወይም የተነጠቀ መሆኑን ነው።በጥቅም ታውረው የሥርዓቱ እኩይ ምግባር ሊታያቸው አለመቻሉና መሣሪያ መሆናቸው እንደሰው ለሚያስቡት ለቅርብ ቤተሰቦቻቸው ጭምር ማፈሪያ ሆነዋል።

በያዝነው ሰሞን የተከሰቱትን ስንዘረዝር የምንጀምረው ብዙዎችን ያነጋገረው ፍትህን በሚጻረረው የኦነግ ኦህዴዱ መንግሥት ፍትሕን ለማረጋገጥ የፍትሕ ሰነድ አዘጋጀሁ ብሎ የቀረበበት ላሙኛችሁ ድፍረቱ ነው።ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው?እንዴትና በማን ተጣሰ? እንዴትና በማንስ ሊረጋገጥ ይችላል? የሚሉት ጥያቄዎች በቅጡ መብራራት ያለባቸው ናቸው።በእኛና በሌሎቹ አገር ወዳዶች በኩል የሚሰጠው ምላሽ ሥርዓቱ የፍትሕ ጠላት እንጂ ፍትሕን ለማስፈን የሚያበቃ ተፈጥሮያዊ ቁመና የለውም የሚል ነው።አድራጎቱ ሌባውን የወንጀለኛ መቅጫ ደንብና አንቀጽ አዘጋጅ እንደማለት ነው። ፍትሕን የጣሰ ወንጀለኛ በፍትሕ መንገድ ይጠዬቃል እንጂ የፍትሕ ባለቤት ሊሆን አይችልም።

የፍትሕ ስርዓቱ በጎሰኞች መዳፍ ውስጥ ወድቆ የበቀል መወጫ መሣሪያ ባደረገ ስብስብ የፍትሕ ሰነድ ይዘጋጃል ማለት ሊያጠቃ የሚፈልጋቸውን ሁሉ ፣አገር የመበታተኑን ዓላማ ጭምር ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት የታሰበ ከመሆን ያለፈ ሌላ ቀና ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም።አገር የዘረፉ፣ሕዝብ የገደሉ፣ ያጋደሉ፣ያፈናቀሉ ስብስቦች የፍትሕ ጠበቃ ሆነው ብቅ ሲሉ ከማዬት የበለጠ ውርደት የለም።ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ማለት የዚህ አይነቱ ድፍረት ነው።ወንጀለኞችን በእርቅ ስም የሚለቅ ወንበዴ ቡድን ፍትሕን ለማስፈን ሰነድ አዘጋጃለሁ ብሎ ሲመጣ ዝም ብሎ ማዬት በቀጣዩ ሊያደርግ ያሰበውን ጥፋት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ነው።ስለሆነም የፍትሕ ሰነድ በሕዝቡ ፍላጎትና ተሳትፎ፣ በሕግ አዋቂዎች እረቆ የሚቀርብና የሚጸድቅ እንጂ ከላይ ወደታች የሚወርድ ትእዛዝ መሆን የለበትም።ለዚያም ነው የማህበረሰብ ፍትሕ(Social justice) ይስፈን የሚባለው።ሥልጣን ላይ በተቀመጠ ቡድን የሚዘጋጅ የሕግ ሰነድ ለሕዝቡ ሳይሆን ሕዝቡን ሰጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት የሚረዳ መሳሪያ ማለት ነው።

ይህንኑ ዝባዝንኬ የፍትሕ ሰነድ ዝግጅት ስርዓቱ በመረጣቸው የብሔራዊ ምክክር ተብዬው ወይም የፓርላማ መንጋ ቡድን እንዲሳተፍበትና እንዲቀበለው የማድረግ ሂደት እንዳለ ሾልኮ የወጣው መረጃ ያረጋግጣል።ሁለቱም አካላት የሥርዓቱ ሹመኞች እንጂ የነጻ ሕዝብ ወካዮች አይደሉም።በሁለቱም ድንኳኖች የተሰገሰጉት ግለሰቦች አብዛኛዎቹ በጎሳ ማንነት የሚያምኑና፣ከዬጎሳው ተመልምለው የመጡ፣ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ቢኖሩም እነሱም ያለውን ሥርዓት የተቀበሉና የጎሳ ፖለቲካ ማራመጃ በሆነው ሕገጥፋት ምለው የተገዘቱ ናቸው።ከነዚህ ጎራ እውነተኛ ፍትሕ አይጠበቅም።ስለሆነም ለእውነተኛ ፍትሕ ከስርዓቱ ጋር ያልተነካኩ፣ በሙያው ዕውቀት ያላቸው፣ከሕዝቡ የተውጣጡ፣ ከማህበራዊ ተቋማት የተወከሉ ሊሳተፉበት ይገባል። በነዚህ የረቀቀው ሰነድም ለውይይት ቀርቦ ሕዝብ ሃሳብ እንዲሰጥበት ማድረጉ ለጥራቱና ለተቀባይነቱ ማረጋገጫ ይሆናል። ከዚህ ውጭ የሚረቅ የፍትሕ ሰነድ ሊባል አይችልም።በሰብአዊ መብት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱት ድርጅቶችና ስብስቦች የሽግግር ፍትሕ እንዲሰፍን ጥሪ ያደርጋሉ።የተበደለ የሚካስበት፣በዳይ ይቅርታ የሚጠይቅበት፣ወንጀል የፈጸሙ ቅጣት የሚያገኙበት ሕግ ይኑር ይላሉ።ይህ ግን እውነተኛ ፍትሕን ሙሉ ለሙሉ ሊያረጋግጥ አይችልም። ፍትሕ በካሳና በይቅርታ ወይም በቅጣት ብቻ የሚረጋገጥ ሳይሆን ችግሩ ዳግም እንዳይከሰት ዘላቂ መፍትሄ ለመፍጠር ከምንጩ መታዬት አለበት።ላለው የፍትሕ ጥሰት ምክንያቱ በሥልጣን ላይ ያለው ጎሰኛ ስብስብ የሚያራምደው ፖለቲካና የሚከተለው የጥፋት መመሪያው ነው። ስለሆነም ሥርዓቱ በካሳ፣ጥቂቶቹን በመቅጣትና በይቅርታ ተሸፍኖ እንዲቀጥል መደረግ የለበትም።ለዘላቂ ፍትሕ የፍትህ ጸር የሆነው የጎሰኞቹ ስርዓት፣ከኋላ ቀር ባህልና ልማዱ ጋር መወገድ ይኖርበታል።

ይህ በእንዲህ እያለ የኦሮሙማው ቡድን አዲስ አበባን ለመዋጥ ባለው ዓላማ ዳርዳሩን እዬቦረቦረ የማመንመኑን በከቦ የመያዝ ስልቱ አምስት የአቅራቢያ ወረዳዎችን ሸገር በሚል ስም አዋቅሮ በአባ ገዳዎች የሚመራ ቡድን ያዘጋጀውን ፍኖተ ካርታ የቃል ኪዳን ሰነድ ብሎ መፈራረሙን የሰማንበት ሳምንት ነው። አሁን እንደ አዲስ ቀረበ እንጂ አዲስ አበባን የመሰልቀጡ ዓላማ ከተጀመረ ዓመታት አስቆጥረዋል።ፊንፊኔ በሚለው ስያሜ ተጀምሮ አሁን ሸገር ማለቱ አዲስ ነገር አይደለም።ደግመን ደጋግመንም ያጋለጥነው ጉዳይ ነው። አውቆ የተኛን ቢጠሩት ወይ አይልም ሆኖ እንጂ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የሴራውን ገፈት መቅመስ ከጀመረ ሰንብቷል።እስክንድር ነጋና ሌሎቹ የባልደራስ ፓርቲ አባላት ከተረኛው አገዛዝ ጋር ተናንቀው ብዙ መከራና እስራት የተቀበሉት ይህንኑ ሴራ በማጋለጥና የአዲስ አበባን ማንነት ለማስከበር ነበር። የነእስክንድር ነጋ ትግል ሰሚ በማጣቱ ለገዢው ተረኛ የኦነግ ቡድን በዬትምህርት ቤቱ የኦነግን ባንዲራ እንዲሰቀልና የጥላቻ ዘረኛ መዝሙር እንዲዘመር ግዳጅ ለመጣል አስችሎታል።ይህንን የተረኞች ድፍረት ጥቂቶች በተለይም በአስርታት የዕድሜ ጣራ ውስጥ ያሉ ህጻናት ሳይቀሩ ተቃውመው ለመከራና ለእንግልት ተዳርገዋል፤በፖሊስ ድብደባ የቆሰሉት

ለተጨማሪ የሕክምና ወጭ ሲዳረጉ፣ከ30 የሚበልጡ ደግሞ በዪእስርቤቱ ተወርውረው ብዙ ስቃይ ደርሶባቸዋል።ከሳምንታት እስራት በኋላ እንደ ጥፋተኛ በ3,000 ሽህ ብር የገንዘብ ዋስትና እንዲለቀቁ በካንጋሮው ችሎት ቢፈረድም ፖሊስ እምቢ ብሎ እስከፈለገበት ጊዜ ድረስ ያሻውን ለማድረግ ችሏል። ከብዙ ውጣውረድ በኋላ ከእስር ቤት የተለቀቁ ቢሆንም አድማ ቀስቃሾች የተባሉት ተማሪዎች ከትምህርታቸው ታግደዋል።ብዙሃኑ ተማሪ በነዚህ ጓደኞቹ ላይ የደረሰውን መከራና ከትምህርት ገበታ መታገድ መቃወምና ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ ሲገባው የጠፍ ዶሮ አድርጓቸው ድምጹን አጥፍቶ መማሩን ቀጥሏል። እንዲህ አይነቱ ፍርሃትና አድር ባይነት የህብረተሰቡ መገለጫዎች በመሆናቸው ለሥርዓቱ የፈለገውን ለማድረግ የሞራል ጉልበት ሆኖታል።

በሌላውም በኩል ኦሮሞ ያልሆኑት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ለታቀደው የሸገር ከተማና ለአብይ አህመድ ቤተመንግሥት ግንባታ ለዓመታት የኖሩበት ቤታቸው እዪፈረሰ ሜዳ ላይ ፈሰው ለችግር መጋለጣቸው አሁንም ድረስ በስፋት ቀጥሏል።ቢጮሁ ሰሚ አላገኙም።የምታጠባ እናትና ህጻናት ፣ደካማ ሽማግሌዎች መጠጊያ አጥተው ለብርድና ለሃሩር ተጋልጠዋል።ቁጥራቸውም ከእለት ወደ እለት እየጨመረ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ሆነዋል።ሌላው የከተማው ነዋሪ ለነዚህ ወገኖቹ ድጋፍ ማድረግ ሲገባው ወንጀሉን በወሬ እዪተቀባበለ ቡና መጠጫ አድርጎታል።አንዱ ለሌላው አለመቆሙ ብቻ ሳይሆን ድርጊቱን አለማውገዙ በራሱ በአገራችን ሕዝብ የአብሮነትና ሰብአዊነት ስሜት ገደል መግባቱን ማሳያ ነው።የፖለቲካ ድርጅቶች ተደብቀው በብጣሽ ወረቀት መግለጫ ከማውጣት ባለፈ ሕዝቡን አስተባብረው አደባባይ ወጥተው ም ሆነ በአዳራሽ ሰብስበው ለማውገዝ አልደፈሩም፣አንዳንዶቹም እንደማይተማመን ባልንጀራ በዪመንፈቁ የጋራ ግንባር መስርተናል እያሉ ሲጨባበጡ ከማዪት በቀር ለምን ዓላማ ፣በምን የፖለቲካ መስመር እንደተስማሙ ግልጽ አላደረጉም።ከትግሉ ይልቅ ለሚያገኙት ድጎማ የሚጨነቁ ሆነዋል።የሃይማኖት ተቋማትም እንዲሁ ለግፉአን ድምጽ አልሆኑም።

እስከ ዛሬ ድረስ በተደጋጋሚ ድረሱልን የሚለው ጥሪ ምንም ፋይዳ ስለማይኖረው ለችግር የተጋለጡት ወገኖቻችን ያላቸው ብቸኛ አማራጭ  ስርዓቱን  ባላቸው አቅም መታገል ብቻ ነው።ጎረምሳና ብርቱ የሆነው ደካሞቹን ከአደጋ እዪጠበቀና እዪሰወረ ባለው መሳሪያ፣መሳሪያ ባይኖረው ከጠላቱ እዪማረከና እዪዘረፈ መቋቋም አለበት።እንደ አቅመ ደካሞችና አካለጎደሎቹ እራሱን ይዞ እዪዬ ማለት ያሳፍራል። ዶሮ ባቅሟ ጫጩቶቿን ከጩልሌ በክንፏ ትከላከላለች።ሌላው በዪመሸታ ቤቱ አልኮል እየተጋተ ማውደልደሉን ፣ጫት ማኘኩንና ሲሻ መምጠጡን ትቶ ለህልውናው መታገል ይኖርበታል።አገርና ሰላም ሳይኖር አጉል ልማዱንና ሱሱን ሊወጣ እንደማይችል ሊያውቀው ይገባል።  በተጨማሪም ምንም እንኳን ሰሚ ጆሮ ባይኖራቸውም  በውጭና በአገር ውስጥ ለሚገኙት ለዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተቋማት፣ለውጭ አገር የዲፕሎማሲ ተወካዮች፣ለኤምባሲዎች የመንግሥትን ኢሰብአዊ ድርጊት ማጋለጥ ተገቢ ነው።ይህንን የሚያቀነባብሩ አገር ወዳዶች ከጎናቸው እንዲቆሙ ጥሪ እናደርጋለን፡ከዚያ ጋር ተያይዞ አቅም በፈቀደ መጠን ግፈኛውን ስርዓት በማሶገዱ ትግል መሳተፍ የዘለቄታ መፍትሔ ነው። በአይሁድ ተስፋፊዎች መኖሪያ ቤታቸው እዪፈረሰ፣መሬታቸው እዪተነጠቀባቸው ሳይፈሩ ፣ታንክና ሚሳይል እንዲሁም ድሮን ከሚጠቀመው የጦር ሃይል ጋር በድንጋይ ውርወራ ፊት ለፊት ከሚገጥሙት ከፍልስጤማውያን ትምህርት መቅሰም ይገባል እንላለን።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዲት ወጣት ግድያ ምክንያት የተቀጣጠለው የኢራን ሴቶችም ትግል አንዱ ምሳሌ ነው። የብዙ አገሮችን ሕዝባዊ ትግል መጥቀስ ይቻላል። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከነሱ በባሰ ስቃይ ላይ ይገኝ እንደሆነ እንጂ ባነሰ ችግር ውስጥ አይኖርም።ሥርዓቱን ታግሎ መጣል ፍትሓዊነት ነው። ፈሪን ልጅ እናቱም አትወደውም ይባላልና ሌላው እንዲደርስለት የችግሩ ሰለባ የሆነው የትግል ምሳሌ መሆን አለበት።ቁጭ ብሎ፣ ማንንም ሳይበድልና ወንጀል ሳይፈጽም የሰው ልጅ በሚገደልባት አገር ለመብትና ለእኩልነት ታግሎ መሞት ህያውነት ነው።

የኦሮሙማው አገር አጥፊ ቡድን ለድፍረቱ ገደብ አጥቶለታል።በጉልበት የሚያደርገውን ቀስ በቀስ እያለማመደ በሕግ ለመከላከል በመንግሥት ተቋማት ሳይቀር ባንዲራውን እያንጠለጠለ መጥቷል። በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 13 የከተማ አስተዳደር ቢሮ ግቢ በግራና በቀኝ የፌዴራል ተብዬውን ባንዲራ አውርዶ በኦነግ ባንዲራ መተካቱ አንዱ ማስረጃ ነው።ነገ በመላ አዲስ አበባ የመንግሥት ተቋማት ግቢ፣ሆቴሎች በራፍና ትልልቅ ህንጻዎች አናት ላይ ላለመሰቀሉ ዋስትና የለም።ውሃ ሲወስድ እያሳሰቀ ነው ይሏል ይህ ነው።ይህች አካሄድ  ከሽመልስ አብዲሳ ቁማሩን በልተናል ከሚለውም ትርክት ወንዝ የምትጨለፍ ጠብታ ናት።ዝም ከተባለ በቀጣይ አዲስ አበባን  የኦነግ የፖለቲካ ቁሻሻ እንደሚያጥለቀልቃት አያጠራጥርም።በአገሪቱ ሰማይ ላይ የተንጠለጠለው ጥቁር የፖለቲካ ደመና የሚያሳዩውም ይህንኑ ነው።ሳይቃጠል በቅጠል!

ባለፈው ሳምንት የተደረገውን የአማራ ክልል ተብዬ የብልጽግና ስብሰባ ተከትሎ በዚህኛው ሳምንት የኦሮሞ ክልል ተብዬው የብልጽግና ጀሌ በናዝሬት ከተማ  የሁለት ቀን  ስብሰባውን አካሂዷል።በዚህ ስብሰባ ላይ የኦነጉ ክንፍ በባሕርዳር የገጠመው ቅሌት እንዳይገጥመው ብዙ ዝግጅትና ጥንቃቄ አድርጓል።ሆኖም ግን እንዳሰበው አልሆነለትም።የሽመልስ አብዲሳ አመራር በክልሉ ውስጥ ብዙ የልማት ዘርፎችን እንደዘረጋ፣ጥጋብና ተስፋ የፈነጠቀበት ክልል እንደፈጠረና ይህም በሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች  አድናቆት ያገኘ መሆኑን በኩራት ሲገልጽ በሌላው በኩል ሰላም እንደሌለው፣ሕዝቡ ለሰላም እጦትና ለድህነት እንደተጋለጠ የሚያወሱ አስተያዬቶችም ተደምጠዋል።ይደግፈናል ብለው ካሰቡት ከአማራው ክልል ሳይቀር ትችት ተሰንዝሯል።የአማራውን ክልል መሪ ይልቃልን ስለአዲስ አበባ ማንነት ክልሉና  እሱ በግሉ ምን አቋም እንዳለው  ሲጠዬቅ አቋማችን በሕገመንግሥቱ ላይ የሰፈረው ነው በማለት ለማምለጥ ሞክሯል።ይህ ማለት ግን ከኦነግ ብልጽግና የተለዬ የፖለቲካ አቋም ይዟል ማለት አይደለም።ይኸው ጅላጅል ብልጥ ቢሆን ኖሮ  ሽመልስ አብዲሳንና  የክልሉን አመራር በወልቃይትና በራያ ላይ ምን አቋም አላችሁ? ብሎ በመጠዬቅ የተኩስ መልስ በሰጠ ነበር።ለዚያ ያልታደለ  መሆኑንና ከነሽመልስ በኩል ሊሰጠው የሚችለው መልስም እሱ ከሰጠው ምላሽ እንደማይለይ እናውቃለን።ሆነም ቀረም እነሽመልስ አብዲሳ ጥርስ የነከሱበትና ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም ብለው እንዲዘጋጁ የማስጠንቀቂያ ደወል የሰሙበት ስብሰባ ነበር።

ሰሞኑ የስብሰባ ጋጋታ የታዬበት ነበር።ከክልሎች ስብሰባ ቀጥሎ ዕሮብ እለት የሁለቱ ምክር ቤቶች ማለትም የሕዝብ ምክርቤትና የክልል ምክር ቤቶች በአንድ ላይ የተሰበሰቡበት ቀን ነበር።በዚህ ስብሰባ ላይ የቀረበው ዋና አጀንዳ የንብረት ታክስ ክፍያ በሕግ እንዲጸድቅ ለማድረግ ሲሆን የስብሰባውን መድረክ የተቆጣጠረው ሽመልስ አብዲሳ ነበር።የንብረት ታክሲ ለክልል ወይስ ለከተማ አስተዳደር ይግባ? በሚለው ላይ የተለያዩ ሃሳቦች የቀረቡ ቢሆንም ለከተማዎች ይግባ የሚለው የውሳኔ ሃሳብ በአራት ተቃውሞና በአምስት ድምጸተአቅቦ፣በአብዛኛው ድጋፍ ሊያልፍ ችሏል።ይህ ውሳኔ ተግባራዊ ከሆነ በመጀመሪያ ተጠቂ የሚሆነው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ኦሮሞ ያልሆነው ዜጋ በተለይም አማራው  ነው።የማይፈልጉትን ለማሶጣት የንብረት ታክሲውን በማይችለው መጠን ቆልለው ይጠቀሙበታል።ቀደም ሲል በንግድ ቤቶች ላይ የኪራይ ጭማሪ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በወር 150 ብር ይከፈልበት የነበረው የቤቶችና ኪራይ ወይም የቀበሌ ቤት በወር 30,000 ብር እንዲከፈልበት ሲወሰን  መክፈል ባለመቻላቸው ብዙ ወገኖች ከሥራ ገበታ እንደራቁና ለችግር እንደተጋለጡ፣አንዳንዶቹም በብስጭት የታመሙና እራሳቸውን ያጠፉ መኖራቸው አይዘነጋም። ደጋግመው አቤት ቢሉም ሰሚ አላገኙም፤ በተለይም ግፉ የጎላው ኦሮሞ ባልሆኑት ላይ ነው።የንግድ ቤታቸውን ለመሸጥ ቢያስቡም የከባቢው አስተዳደር ዋጋውን የምንወስነውና ገዥውንም አወዳድረን የምናቀርበው እኛ ነን በማለት እንዳይሸጡም እንዳይለውጡም መብታቸውን ተገፈዋል።ይባስ ብለውም ያልተከፈለ ጉርድ  ወይም የግብር ማስተካከያ እዬተባለ ለዳግመኛ  ክፍያ ተገደው ምንም እንዳኖራቸው

ማድረጉ ከወለጋው ዘረፋና ማፈናቀል ጋር ተመሳሳይ ሆኗል። በሌላም መንገድ ከዓመታት በፊት በሊዝ የተያዘ ቦታ በአሁኑ ዋጋ እንዲከፈልበት ተደርጎ ገንዘብ መዝረፉ አንዱ የስርዓቱ መበዝበዣ ዘዴ ሆኗል። የአሁኑም የንብረት ታክስ ለዚሁ ዓላማ እንደሚውል ቅንጣት ያህል አንጠራጠርም።ቀደም ሲል መለስ ዜናዊ አዲስ አበባ ደሃ የሚኖርባት ከተማ አትሆንም ያለውን አስታውሰን  የአብይ አህመድን መኖር ያልቻለ ከከተማዋ ለቆ ይውጣ የሚለውን  ሃሳብ ስንጨምርበት ከተማዋን ከማጽዳት ቅድመ አሳብ የመነጨ መሆኑን እንረዳለን።የሰበርናቸውን ሰብረናቸዋል፣ካልፈቀድንላቸው የትም መኖርና መንቀሳቀስ አይችሉም የሚለውም ዛቻና ፊከራ ለዚህ መንደርደሪያ ነው።

በዚህ  በሁለቱም ምክር ቤቶች ጥምር ስብሰባ ላይ ዓይናችን ያዬው ጉድ ብዙ ቢሆንም በተለይ  ዲማ ነገዎ የተባለው የኦነጉ መሪ አማርኛ እንደማያውቅና እንደማይገባው የውጭ አገር ታዛቢ ይመስል የትርጉም መሣሪያ አናቱ ላይ ተሸክሞ መዋሉን ነው።እሱን ከተመቸው የጦር ሜዳ የብረት ቆብም ተሸክሞ ቢቀመጥ የራሱ ምርጫ ነው።በዚህ ብቻም አያልቅም ይህ የሰማንያ ዓመት አጁዛ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ  ለስብሰባ ስነስርዓት ባዳ መሆኑን  ማስቲካ እንደ ልጅ ማመንዠኩን ስናይ ቆሜለታለሁ የሚለውን ሕዝብ መናቁ  አሳዝኖናል።ይኸው ጉደኛ ከ33 ዓመት በፊት በጀርመን አገር በተደረገ ስብሰባ ላይ ኦሮሞ ያልሆነው በሙሉ ከ አዲስ አበካ(ከፊንፊኔ) ከተማ ተጠራርጎ ወደመጣበት ይመለሳል ሲል በግልጽ ተናግሮ ነበር፤አሁን ኦነግ ብልጽግና የሚያደርገውም ይህንኑ ነው፤ዲማም የዚያ አስፈጻሚ ሆኖ ከጀርባ ይዘውራል።ከሰላሳ ዓመት በፊት ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት በነበረበት ጊዜ የማስታወቂያ ሚንስትር ሆኖ የሚናገረውና የሚጽፈው በአማርኛ ነበር።አሁን ግን አማርኛ የማይሰማ የማይለማ ሆኖ ለመታዬት ሞከሯል።ይህ ነው ዓላማ ቢስና ሃቀኝነት የሌለው ፖለቲከኛነትና የፖለቲካ አቋም። በዚህ ድርጊቱ  በጭፍን የኦነግ ተከታዮች በኩል ሊያስቆጥር የሞከረው ነጥብ አማራንና አማርኛን በተለይም ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚጠላ በማሳዬት ነው።በጣም የሚገርመው ደግሞ በሱ ሰልጥኖ የክልሉ መሪ የሆነው ሽመልስ አብዲሳ ከሱ ባላነሰ አማርኛ በሚናገርበት ስብሰባ ላይ መገኘቱ ነው።አድራጎቱ ምናልባት በኦሮሙማው ካምፕ ውስጥ ያለውን የጥቅምና የሥልጣን ንትርክ ተከትሎ የመጣ  ንቀት የሚያሳይ እድምታም  አለው ብለን እንገምታለን። ያም ሆነ ይህ ግን ሁሉም የኦሮሙማው የኦነግ ቤተሰቦች በጥቃቅን የጥቅምና የሥልጣን ምክንያት እርስ በርሳቸው ቢሻኮቱም ኢትዮጵያን በማፈራረሱ ላይ አንድ ናቸው።

አዲስ አበባ ካሳ ትክፈል የሚለው አባባል የኦሮሞን ሕዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ በሚለው ሽፋን የዘረፋ ምህዳሩን ለማስፋት እንጂ ለሕዝቡ አስበው አይደለም።በአዲስ አበባ አካባቢ የሚኖረው  ደብረዘይትም ሆነ ናዝሬት ወሊሶም ሆነ ሆለታና አምቦ፣ሱሉልታም ሆነ ሰበታ ነዋሪ የኦሮሞ ተወላጅና ሌላው ዜጋ ለአዲስ አበባ በቅርብ እርቀት ላይ በመኖሩ ከሌላው ሕዝብ በተሻለ መንገድ የአዲስ አበባ ተጠቃሚ ነው።ሕክምና ቢፈልግ፣ያመረተውን ለገበያ ቢያቀርብ፣ልጆቹን ለከፍተኛ ትምህርት መላክ ቢፈልግ፣ ተቀጥሮ ለመሥራት--- ወዘተ አዲስ አበባ በሯን አልዘጋችበትም።በቀላል ወጭ  መጓጓዣ ተጠቅሞ ወይም በእግሩ ተጉዞ ያሰበውን አድርጎና የፈለገውን አግኝቶ የሚመለስባት ከተማ ነች።ደብረዘይትም ሆነ ናዝሬት፣ወሊሶም ሆነ ሆለታ አምቦም ሆነ ሱሉልታና ቡራዩ ነዋሪ ከደሴና ፣ከባህርዳር ከጎንደርና ከደብረብርሃንና መንዝ፣ከወለጋና ኤሉባቦር፣ከጅማና ባሌ፣ከሃረርና ከቦረና ካለው ሕዝብ በተለይም ኦሮሞ ለከተማዋ በመቅረቡ የተሻለ ተጠቃሚ ነው።ስለዚህ በአዲስ አበባ ዙሪያ ላሉት የኦሮሞ ተወላጆች ልዩ ጥቅም  ይኑራቸው የሚለው ጫጫታ አይሰራም።ልዩ ጥቅም ይኑረው ከተባለ አዲስ አበባ ከተማን በእውቀቱ፣በገንዘቡ፣የገነባው ሁሉም ኢትዮጵያዊ የባለቤትነት ድርሻ አለው።በይበልጥም የከተማዋ ነዋሪ አዲስ አበቤ!

በቀጣዩ ሃሙስ ቀን የአዳነች አቤቤም የከተማው አስተዳደር ስብሰባ አድርጓል። ይህም ካለፉት ስብሰባዎች ጋር ተጣምሮ የተረኞቹ የአነግ ብልጽግና ቡድን ለቀጣዩ እርምጃ መንደርደሪያ እንደሆ ተደርጎ መታዬት አለበት።በስብሰባው ላይ በዋናነት የቀረበው አጀንዳ የአዲስ አበባን የስርዓተ ትምህርቱን መመሪያ የሚመለከት ነበር።አነግ በአዳነች አቤቤ በኩል ሊጭን የሞከረው የባንዲራና የጥላቻ መዝሙር በተማሪዎች፣በመምህራኑና በወላጆች ተቃውሞ ሲከሽፍ በሌላ በኩል የሚፈልጉትን ለመጫን ሲሉ የትምህርት ፖሊሲውን እንዲያወጣ በሚል ሽፋን የመደቡት የኦሕዴድ አባላት በሚቆጣጠሩት የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ በኩል ነው።በጥናት ተዘጋጀ የተባለው የትምህርት ፖሊሲ ስለባንዲራና መዝሙሩ ያለው ባይኖርም እስከስድስተኛ ክፍል ድረስ ልጆች አፍ በፈቱበት ቋንቋ እንዲማሩ ሆኖ ሌላ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲማሩ ይመክራል፣አማርኛ ተናጋሪው ኦሮሚኛ፣ኦሮሚኛ ተናጋሪው አማርኛ ሌሎቹም እንዲሁ።ከሰባተኛ ክፍል በላይ ሁሉም ትምህርት በእንግሊዝኛ የሚሰጥ ሲሆን የዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ፈረንሳይኛና አረብኛ እንዲማሩ ሃሳቡን ሰጥቷል።

በመጀመሪያ ደረጃ ቋንቋ መማር ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፣ያም በፈቃደኝነትና በፍላጎት መሆን አለበት።የነአዳነች አቤቤ አሠራር ግን በዋናነት የኦሮሞውን የበላይነት በቋንቋውም በኩል ለማረጋገጥ ነው።በባንዲራና በመዝሙሩ በፊት በር ያልተሳካላቸውን በጓዳ በር በስርዓተትምህርት ሰበብ ይዘው መግባታቸው እንደሆነ ይሰማናል። ለኢትዮጵያኑ የማያውቁትን ቋንቋ የመማሩ ፍላጎት በአነግ የሚጀመር ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በኖሩበት አካባቢ የሚነገረውን ቋንቋ ተምረው በመናገር ተግባብተው፣ተጋብተውና ተዋልደው መኖር የቻሉ ናቸው።ያም ከሁለት በላይ ቋንቋ ተናጋሪ ለሆኑ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ልጆች መወለድ ምክንያት ሆኗል።የአገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚማሩበት ቢኖር ጥሩ ነው፤ማንም አይጠላም። ቀደም ሲል በንጉሡ ጊዜ የውጭ አገር ቋንቋ ትምህርት ቤቶች ለምሳሌም የጣሊያን፣የፈረንሳይ፣የጀርመን ነበሩ።

በአገር አቀፉ የትምህርት ካሊኩለም መሰረትም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፈረንሳይ ቋንቋ ትምህርት አንዱ ነበር።የእንግሊዝኛ ቋንቋን በተመለከተ በንጉሱ ጊዜ ፤በሃምሳዎቹ ዓመት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ በክፍለ ጊዜ ይሰጥ ነበር።አንደኛና ሁለተኛ ክፍል ግሪን ፕራይመር(Green Primer)፣ ከዛም ሪደር ዋን(Reader One)፣ ሪደር ቱ(Reader Two)፣ ሪደር ስሪ(Reader Three)፣--እያለ ይቀጥላል።ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ ሁሉም ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነበር።የሂሳብ የቀጭኔ ስዕል ያለበት ሃይወይ አርትሜቲክስ(Highway Arithmetics)መጽሃፍ፣ በታሪክ በኩልም የሰው ልጆች ታሪክ (History of Man፣የጆግራፊም የአገራት አቀማመጥ፣የከተማዎች ስምና የሕዝብ ብዛት፣የታላላቅ ወንዞችና ተራራዎች ስምና አድራሻቸው፣የካርታ ንባብ(Atlas and map reading)፣ስምንተኛ ክፍል የዓለም ታሪክ (world History)የሚለው ጠብደል መጽሐ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።ከስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በኋላ ልዩ ልዩ ኮርሶች የመግባት ዕድል ነበር።ስለሆነም በዚያን ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እንግሊዝኛ የመስማትና የመናገር ብቃት ነበረው።በ1956 ዓም ጀምሮ ከአንደኛ እስከስድስተኛ ክፍል ድረስ ሁሉም ትምህርት በአማርኛ እንዲሆንና አጠቃላይ ፈተናም (ሚኒስትሪ)እንዲወሰድ ተወሰነ፣ከሰባተኛ ክፍል በላይ በነበረው እንዲቀጥል ሆነ፣ከዘጠነኛ ክፍል በላይ የሙያ ትምህርቶች የተካተቱበት የቮኬሽናል ትምህርት ተጀመረ። ይህንን ለማስረጃነት ያቀረብነው የውጭ ቋንቋ በተለይም እንግሊዝኛ የማስተማሩ እቅድ በዘመነ አነግ የሚጀመር አለመሆኑን ለማሳዬት ነው።ስለአረብኛ ቋንቋ ማወቅ አስፈላጊነት የተሰጠው ምክንያት ኢትዮጵያውያን የአረቦች ገረድና አሽከር ሆነው የመኖራቸውን መጥፎ ዕድል በቋሚነት ከመቀበል የመነጨ ሆኖ አገኘተነዋል።ብዙ ወጣቶች ለሥራ ወደ አረብ አገር ስለሚወጡ የቋንቋ ችግር እንዳይገጥማቸው ሲባል ነው የሚል ምክንያት ተሰጥቷል።ለዜጎቹ የሚያስብ አካል ቢሆን ኖሮ ምክንያቱን ከስደት ጋር ሳይሆን ከእውቀት ጋር ባያያዘው ነበር።በተጨማሪም

ከስደትና ከባርነት ወጥተው በአገራቸው ላይ ተደስተው ሊኖሩ የሚችሉበትን መንገድ ማቀድ በተገባ ነበር።

ሌላው የሚነሳው ጥያቄ እያንዳንዱ የከተማም ሆነ የክልል አስተዳደር የራሱን የትምህርት ፖሊሲ ይቅረጽ ከተባለ የትውልዱ የእውቀት ደረጃ ተመጣጣኝነቱ እንዴት ሊረጋገጥ ይችላል?መበላለጥ አይኖርም ወይ?የአገሪቱ የትምህርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱስ ምን ሚና ይኖረዋል?ሁሉም በዬፊናው በመረጠው መንገድ ይሂድ ከተባለ የዕውቀት መስኩን የጨረባ ሰርግ ድንኳን አያደርገውም ወይ?በሰለጠኑት የአውሮፓም ሆነ የእስያ አገሮች የትምህርት ፖሊሳቸው አንድ ወጥ ነው።በቋንቋቸው ያስተምራሉ፣ ያም ላሉበት ደረጃ አበቃቸው እንጂ አልጎዳቸውም።ምን ማስተማር እንደሚገባ ማወቁ እንጂ በምን ቋንቋ መማሩ ወሳኝ አይደለም።ለምርምርና ከውጩ ዓለም ጋር ለመግባባትም ዓለም አቀፍ የሆነ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣሉ እንጂ የራሳቸውን ቋንቋ የድንቁርና መነሻ አድርገው አይቆጥሩትም። እንግሊዝኛን ወይም ፈረንሳይኛን የእድገት መንገድ አድርጎ ማዬት ስህተት መሆኑን በቋንቋቸው የሚማሩትን አገሮች ማዬቱ በቂ ነው።ቋንቋቸውን ጥለው የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑት የቅኝ ተገዢ አገሮችን በተለይም የአፍሪካን ማዬቱ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት እንዳላወጣቸው ማስረጃ ነው።የሰው ወርቅ አያደምቅ !

ወደ ሌላው እርእስ ስናመራ የወያኔና የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የሥልጣን ክፍፍል መጠናቀቁን የሚያወሳው ጉምጉምታ እንደሚያሳዬው ከሆነ ደብረዮን ምክትል ጠ/ሚኒስትር፣ ደመቀ መኮንን የተባለው አጋሰስ በተባበሩት መንግሥታት ቋሚ ተጠሪ፣የደህንነቱና የመረጃ ቢሮ ሃላፊ ጥሩነህ ተመስገን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ፤ የጦር ኤታ ማጆሩ ብርሃኑ ጁላ አምባሳደር ሆኖ  በምክትሉ በአበባው ታደሰ እንደሚተካ፣የወያኔው ጌታቸው ረዳ የአብይ አማካሪ ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ ወጥቷል።ያንን ተከትሎ ብዙ ሹም ሽረቶች ተካሂደዋል።ከነዚያም ውስጥ በፌዴራል ደረጃ የሚኒስር ምክርቤት ወይም የካቢኔ አባላት የሆኑ አራት ባለስላጣናት ከቦታቸው ተነስተዋል።ከነዚያም ውስጥ በሌብነትና በሙስና የሚታወቀውና ክስ የቀረበበት ታከለ ኡማ፣የሱ አውታንቲ የነበረችው ዳግማዊት ሞገስ፣አቶ ኡመር ሁሴንና አቶ ተፈሪ ፍቅሬ አብይ አህመድ በተገኘበት ስንብት ተደርጎላቸዋል። የሚገርመው ታከለኡማ ለትምህርት ሲል እንደለቀቀ ተደርጎ  መነገሩ ነው።እዬተቀጣጠለ የመጣው የሕዝብ እምቢተኛነት ያስከተለው ነውጥ ለመሆኑ የሚካድ አይደለም፤ገና ብዙ መተራመስና የእግሬ አውጭኝ ሩክክር መቀጠሉ አይቀርም።ሁሉም ባለሥልጣን በዘረፈው የሕዝብ ገንዘብ በውጭ አገር ቤትና ንብረት ስለገዛ መኖሪያውን  አደላድሏል።ጥያቄው ስንቱ አምልጦ ይወጣል የሚለው ነው።እርስ በርሱ የሚገዳደል እንደማይጠፋ ያለው ትርምስና መጠቋቆም ማሳያ ነው።

ለሕዝቡ ሰላምና አብሮነት ለአገርም አንድነት የሚበጀው ሙሉ ለሙሉ የጎሳ ሥርዓቱ መገርሰስ እንጂ የሹመኞች የቦታ መለዋወጥ እንዳልሆነ ሕዝቡ ጉልቻ ቢለወጥ በሚለው የተለመደ ተረት አጣጥሎታል።

በወለጋ የሚካሄደው የንጹሃን ጭፍጨፋ ይበልጥ ተጠናክሯል።የክልሉ ልዩ ሃይል ሳይቀር በመሳተፍ የአማራው ማህበረሰብ ተወላጆች በማንነታቸው እዬተመረጡ  በማለቅ ላይ ሲሆኑ፣ንብረታቸው ይዘረፋል ፤ቤታቸው ይቃጠላል።መውጫ ማምለጫ አጥተው የድረሱልን ጩኸት ቢያሰሙም የሚሰማቸው አላገኙም።በመንግሥት ተብዬው የተሰጠው ምላሽ ይባስ ብሎ የአማራ ሸኔ ወለጋን እያሸበረና ንጹሃንን እዬገደለ ነው የሚል ሆኗል።ይህንን ፍረጃ የአማራ ክልል መሪ ተብዬውም ተቀብሎ አስተጋብቶታል።የጎባጣ አሽከር አጎንብሶ ይሄዳል ሲባል ይኸኛው ግን ከማጎምበስም አልፎ ተንበርክኮ ሲሄድ አይተናል።

ራያና ወልቃይትን ለወያኔ አሳልፎ ለመስጠት የሚደረገው ሴራ ተጠናክሮ ቀጥሏል።የክልሉ አስተዳደር የፋኖ አባላቱን እያደነ፣ልዩ ሃይሉን ከቦታው እያስለቀቀ ለወያኔ በሩን ሲከፍትለት ፣በመከላከያ ስም የኦነግ አሸባሪ ሃይል ዩኒፎርም ለብሶ የቀሩትን የፋኖ መሪዎች ለማደን ተሰማርቷል። ወያኔ ሃይሉን አጠናክሮ ቦታዎችን በመከበብ ለመንጠቅ ዝግጅቱን አጠናቆ እርምጃ በመውሰድ በራያ በኩል ጀምሯል።ለአውሮፓውያንና ለአሜሪካኖቹ እራስ ምታት የሆነው የኤርትራ ሃይል ከትግራይ ወጥቷል ቢባልም የሚታይ ማረጋገጫ ነገር የለም።ወጣም ወረደም የወደፊቱ ሁኔታ ከጦርነት የራቀ አይሆንም። በተለይም የወልቃይት ሕዝብና ፋኖ እስከመጨረሻው የደም ጠብታ ለመዋጋት ቆርጠዋል።ነዋሪውን በችግር እዬቆሉ ማንበርከክ የሚለውም አንዱ ስልት ነው። የአብይ መንግሥት ባንዳ የከባቢ ተወላጆችን በመደለል የከባቢው ሕዝብ ተወካዮች ለወያኔ እንዲሰጥ ተስማምተዋል የሚል ድራማ ማዘጋጀቱ ተሰምቷል።የወልቃይትና ራያ ጉዳይ የአማራው የመኖርና ያለመኖር ፣የህልውና ጥያቄ እንጂ ለቁራሽ መሬት የሚደረግ ትግል አይደለም።ስለሆነም ሁሉም አማራ ለዚህ የማንነት ወሳኝ ትግሉ ተካፋይ ሊሆን ይገባል።

በአብይ የማንብደድ ሥራ የተደሰቱት ምዕራባውያን የገንዘብና የዲፕሎማሲ ድጋፋቸውን ለመቸር፣ በአሜሪካ ኮንግሬስ ተጥሎ የነበረው ተአቅቦ ለመነሳት ዳር ዳር እዬተባለ መሆኑን ሰምተናል።ሁኔታውን ለመታዘብም የጀርመንና የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች ሰሞኑን አዲስ አበባ ገብተው ከአብይ ጋር ተነጋግረዋል።በምን ርእስ ላይ እንደተነጋገሩ ባይታወቅም ወያኔ በቀድሞ ቦታው ተመልሶ በሁሉም ዘርፍ የሥልጣኑ ተካፋይ የሚሆንበትን ለማረጋገጥ እንደሆነ ይከተሉ ከነበረው አቋማቸው መረዳት ይቻላል።በኤፈርት(Effort) በተባለው የዘረፋ ተቋም በኩል ያካበቱትና የተነጠቁት ሃብት የሚመለስላቸው መሆኑም እዬተነገረ ነው።በዘረፋና በልዩ ልዩ ወንጀል የታሰሩትም በመፈታት ላይ ናቸው። ቻይና ፤ሩስያና ኢሚሬትም በበኩላቸው ውርውር እያሉ ነው።አብይ አህመድ የተሻለ ገንዘብ ካገኘ አንዱን በሌላው መፈንገሉ የተካነበት ሙያ ነው።

ያሳለፍነውን ሳምንት ስንገመግመው

የአገራችን ሁኔታ ከድጡ ወደማጡ እዬሆነ መሄዱን ታዝበናል ።የሕዝቡ ብሶት ሊገነፍል የቀረው ጊዜ አጭር ይመስላል።የኑሮ ውድነቱ፣ሰላም እጦቱ፣ቤት እዬፈረሰ ዜጋ ሜዳ ላይ መፍሰሱ፣ የገንዘብ ግሽበቱ፣ የወያኔና የኦነግ ኦሕዴድ ጥምረት ሕዝብ አንቅሮ የተፋውን የኢሕአዴግ አገዛዝ መልሶ የማምጣቱ ሂደት፣ወጣቱን እያሳደዱ ማሰር፣ የምንሊክና የጣይቱን ስዕልና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ በባጃጁ ላይ የለጠፈውን ማሳደድና ማሰሩ መጠናከሩ፣የስብሰባው ጋጋታና የተሰብሳቢው ንቀትና አላዳምጥም ባይነት፤ጥያቄና ተቃውሞው፣ የስርዓቱ መጨረሻው መቅረቡን ያረጋግጣል። በውደቅ አልወድቅም ትግል አገራችን ለከፋ አደጋ እንዳትጋለጥ፣ በሕዝብ ላይ የሚደርሰውንና ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለማስገድ ወይም ለመቀነስ ከአሁኑ ለሕዝባዊ አመጽ ዝግጅት ይደረግ የሚለው ጥሪያችን ነው።

ከሦስት ቀናት በኋላ የሚከበረውን የጥምቀተ ባህር በዓል ምክንያት በማድረግ በነሽመልስ አብዲሳ በኩል የወጣው አምባገነናዊ ትዕዛዝ ለሕዝባዊ አመጹ ክብሪት ሊሆን የሚችልበት ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ባለፈው ዓመት የአምስት ሰዎች ህይወት ለማለፍና ብዙ ሕዝባዊ እልህ እንዲቀሰቀስ ያደረገው የወይበላ ማርያም ታቦት አከባበር እንደሆነ ይታወሳል።ዘንድሮ በባሰ መልኩ መከበር የለበትም የሚል ድፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተሞላበት ትዕዛዝ ተላልፏል።የእስልምና መጅሊሱ ሳይቀር ትክክል አለመሆኑን በመግለጽ የሽመልስን ውሳኔ ተቃውሟል።የሚያመጣውን በጊዜው የምናዬው ይሆናል።

ለአገር አንድነትና ለፍትሕ መስፈን የሚያበቃ ሕዝባዊ አመጽ ይቀጣጠል!